**ጀንፎና ጅና!!**

ዓመት ጠብቀው፤ ዐውደ ዓመትን ዙረው ከሚመጡት በዓላት አንዱ የገና (ልደት) በዓል ነው፡፡ ይህ በዓል በሀገራችን በያመቱ ታኅሣሥ 29 ቀን "ዮም ተወልደ ቤዛ ኵሉ ዓለም" (ዛሬ የዓለም ቤዛ ተወለደ) እያሉ የክርስትና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያኖች በደማቅ ሥነ ሥርዓት በዓሉን ያከብራሉ፡፡ ለገና በዓል በቀረበ ግዜ በሀገራችን ከሚዘወተሩና ከሚወደዱ ክንዉኖች  መካከል የገና ጨዋታ ዋናዉ ነዉ በአሉን መድረስ ተከትሎ ጎብዛዝት መጫወቻዋን ጥንግ የሚያሾሩበት  የክትክታ ዱላ በመቁረጥ በደንብ እንዲጠነክር ቅቤ እያጠጡ ሲወለዉሉት ይቀርሙና የገና በዓል ደረስኩ ደረስኩ ሲል ሰፈሩ ሲደምቅ ጨዋታዉ ሲደራ የክትክታዉ መታያ ቀን ይሆንና  ለገና ጨዋታ የጎበዝ ጥሩር መለጊያ በትርነት ይዉላል። ታድያ ይህ በትር እልህና ጉልበት በተቀላቀለበት ጎዝ እጅ የገባ ለት ጉልበቱ በደንብ የታያል ሆኖም ይምትለጋዋ ጥሩር ጥንካሬ በትሩን ከያዘዉ ጎበዝ ጋር በማበር አቅምና ጥንካሬዉን ይፈታትኑታል መፈታትን ብቻም አይደል በትሩ የማታ ማታ መሰንጠቁ አይቀሬ ይሆናል ታድያ በዚህ ግዜ ለአደጋ ግዜ ተብሎ የተዘጋጀ ከበሬ ጅራት የተቆረጠ ለዱላዉ ማስገቢያ የሚሆን በርጥበቱ የተቆረጠ **ጅና** የሚባል ቆዳ (በዘመናውዉ አስነጋገር ገምባኤ አይነት ማለት ነዉ)እንዲሁም  ከበረት ጥቅል የተዘጋጀ በተለምዶ አጠራር **ጀንፎ** ተብሎ በሚጠሩ  እቃዎች  የመጀመሪያ እርዳታ ይደረግለታል የበትሩ  ስንጥቅ በደንብ እንዲያያዝና ክፍተት እንዳይኖረዉ  በቁልቁአል ደም  እየተሞላ  በጅና  ይወጠራል ከዛም በደንብ እንዲጠነክር በጀንፎ ይታሰራል በዚህ ሁኔታ የመጀመሪያ እርዳታ ይደረግለትና  እስከጨዋታዉ ማብቂያ ድረስ የጎበዝ አለቃ መተማመኛ በትር ይሆናል ጥንጓንም ያጎናታል።

መቸም በዓለ ገና ነዉና ከጅምሬ ስለምን መተየብ እንደፈለኩ ሳትገምቱ አልቀራችሁም። እርግጥ ነዉ ለመኖር ምክንያት የሆነን ለመዳናችን ዳግም የሰዉ ስጋን ለብሶ ወደምድር በበረት ተወልዷል ተብሎ በህዝበ ክርስትያን ዘንድ ይታመናልና ለመላዉ የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳአን አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ በሃገሬ ጉዳይ አንዳንድ እዉቀቶችና መረጃዎችን ለመቃረም በይነ መረብ ላይ ከወዲህ ወዲያ ስል ከረም ያለ በትንቀሳቃሽ ምስል የታጀበ በወርሃ ታህሳስ ግድም በደብረብርሃን ዩንቨርስቲ የተካሄደ  በሙሁራኞች የተሞላ የዉይይት ሃሳቤን ገዛዉና እዛዉ ምልህቄን ጣልኩ። የዚህ ዉይይት ጭብጥ የአማራና ኦሮሞ የህዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ቅኝት ማድረግ ሲሆን ከላይ እንደመንደርደሪያ የሆነችዉን ሃሳብ ከዚሁ ውይይት ላይ በአንድ ሀገር ወዳድ ሙሁር ማጣቀሻ ምሳሌነት የቀረበች ነበረች ዉስጤ ከርታለችና ላጋራችሁ ወደድኩ የፅሁፌ መነሻም መድረሻም ጭብጥ አደረቁአት።

ነገሩ ወዲህ ነዉ ሀገሪቱን በማላብኝነት ለሃያ ሰባት ዓመት በበላይነት ሲዘዉራት የነበረዉ ሕዉሃት መራሹ የኢህአዴግ መንገስት የስልጣን እርካቡን ለማስፋት እንዲሁም መቀመጫዉን በተመች መሬት ላይ በማድረግ ጨለማ ሕልሙን ለማሳካት የመጀመሪያ እንቅፋት ነዉ ያለዉን በኢትዮጵያዉያን ደም ዉስጥ ያለዉን ሕብረ ብሔራዊ  ስሜት፣ ፍፁም መከባበረና የመዋደድ ባህል በማጥፋት በዘርና በጎጥ በመከፋፈል ከሀገር ይልቅ ጎሳ ተኮር አስተሳሰብ በማህበረሰቡ ዉስጥ ማሳደግ ብሎም የተመቻቸ አጋጣሚን በመፍጠር በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ጥላቻን መረሰርት ያደረጉ አስተምሮቶችን በማስፋት አንዱ በሄር ስለሌላዉ ያለዉን መልካም አስተሳሰብ በማጥፋትና ታሪካዊ ትስስሩን ባልተገባ አስተምህሮት በመበረዝ ከዛም ሲያልፍ ለስልጣኔ ስጋት አይሆኑም ያላቸዉን ክልሎች መሳርያ በማስታጠቅ ጭምር ለእርድ ሲያደልብ መክረሙ ያደባባይ ሀቅ ነዉ። ሕዉሃት ኢህአዴግ በተለይ በኦሮሞና በማራ ብሔር ላይ መለያየትን በመፍጠር ሁለቱ ማህበረሰቦች እሳትና ጭድ እንዲሆኑ ስልጣን ከያዘበት ቀን አንስቶ ሲሰራበት ስራቀቅበት ኖሯል እሰከ ቅርብ ግዜ ድረስም ሁለቱ ማህበረሰቦች በእቅዱ መሰረትም የሄዱ እስከሚመስል ድረስ ልዩነታቸዉ ሰፍቶና ጎልቶ ወቶ በአንድ መቆም እንድይችሉ አድርጉአቸዋል ለደከሙትም ማንቂያ ይሆን ዘንድ የአኖሌን ሃዉልት ሳይቀር አቁአላቸዋል።

ምሁሩ ንግግራቸዉን ሲቀጥሉ የአማራና ኦሮሞ ህዝቦች መሰረታቸዉ ጠንካራ በብዙ ታሪክ የታሰረና በአንድነት የብሔር ስሜት የታሸ አንድ ዱላ ናቸዉ የሚጫወትባቸዉ በዛና ተሰነጠቁ ይላሉ። ሕዉሃት ኢህአዴግ ለሃያ አምስት አመታት ይህንን ጠንካራ በትር ለመሰንጠቅ ብሄርተኝነት በሚል ጥሩር ሲለትማቸዉና አንዱን በዳይ አንዱን ተበዳይ በማድረግ ከሚለ ህፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልዩ በጀት በመመደብ ያልተገባ ታሪካዊ አስተምህሮቶችን በመሰንቀር የጎበዝ አለቃ ጉልበት ሆኖ በመሃላቸዉ ያለዉን አንድነት ለመሰንጠቅ ለሁለት ለመክፈል ከዛም ለሁለት የተከፈለዉን በትር መሰል ማህበረሰብ ማገዶ በማድረግ ሀገራችንን ወደማትወጣዉ አዘቅት ለመጨመር ደክሟል ሰርቷል። ይህንን ለማሳካት ብዙ ሺህ ንፁሁአን ዜጎች ደማቸዉ ያለምክንያት ፈሷል። በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር የህዝብ ገንዘብ በከንቱ ፈሷል። ታድያ ይህ ሁሉ ነብስ ያለአግባብ የሚጠፋዉ ይህ ሁሉ ገንዘብ የሚባክነዉ የሚላስ የሚቀመስ አተዉ በየቀኑ እንደቅጠል በሚረግፉባትና የአስከፊ ድህነት ተምሳሌት በሆነችዉ ሀገራችን መሆኑን ልብ ይሏል። ደግሞም ይህ መንገድ ላለፉት ሃያ አምስት አመታት በስኬት ጎዳና በማንፈላለስ በትረ ስልጣኑን ያለተቀናቃኝ የሀገሪቱን አንጡረ ሀብት ያለጠያቂ ሲሰፍር፣ ሲዘርፍ ይበጀኛል ያለዉን ሲጠቅም የጠላዉን ከማዕከላዊ እስከ ሸዋሮቢት ከዝዋይ እሰክ ደደሳ እንዲሁም ስም ያልወጣላቸዉና በፊንፊኔ አዲሳባችን መሃል በድብቅ ተገንብተዉ ንፁኋን ዜጎችን ሲያሰቃይ ሲገድል ቆይቷል ይህ ግፍ ደግሞ በዋናነት በሁልቱ ማህበረሰቦች ላይ ያነጣጠረ ሆኖ ከርሟል። እርግጥ ነዉ ከነዚህ ማህበረሰቦች ጋር በማበር በሕብረብሄራዊ ፅኑ ስሜት የታገሉትን በሙሉ ፍሬን እንደበጠሰ ከባድ መኪና ያለርህራሄ ሲጨፈልቅ ኖሯል አሁንም ቀጥሎበታል። ግና ይህ ሕዝብ እየተገፋም አይተበደለም እየተገደለም በየማሰቃያዉ የዘር ፍሬዉ እይተኮላሸም ጥፍሮቹ በጉጠት እየተነቀሉም በሀገሪቱ ፍትህ ይመጣ ዘንድ በቡድንም በተናጥልም ሲመክር እድሉን ሲያገኝ ሲታገል ኖሯል። ሆኖም የህዉሃት ኢህአዴግ ግፍና ኢ-ፍትሃዊነትነቱን ለማስቆምም ሆነ ለማስታገስ በምክር አልሆነምና በዝክር ሊሉት የአህያ ምንትስ በሆዱ ነዉ እንዲሉ አበው ሕዝብ አላዋቂ ሳይሆን ታጋሽ መሆኑን በተግባር ሊያሳይ በጎንደር ከተማ በሕዉሃት ኢህአዴግ የተሰነጠቀዉን የአንድነት በትር መልሶ ሊገጥም ልክ እንደቁልቋል ደም በጎዳና የፈሰሰዉን የኦሮሞ ወገኖቹን ደም ደሜ ብሎ አጋንንት፣ ተባብተኛ የተባለዉን ወንድሙን አለሁልህ ብሎ የጠራ የተከበረ ዜጋ መሆኑን ሊመሰክር ስንትቃቱን ሊገጥም አደባባይ ወጣ በዛም አጋጣሚ ቡዙኋን በአደባባይ የሞትን መራር ፅዋ እንደ ኦሮሞ ወንድሞቻቸዉ ተጎነጩ። ይህ መራር እዉነታ አፍንጫ ሲመታ እንደሚባለዉ ነዉና የኦሮሞ ሕዝብ አጋርነቱን ዳግም ለማሳየት የተሰነተቀዉን የአንድነት በትር ለማከም ያለዉን ቁርጠኘንት በአዳማ ላይ በነቂስ በመዉጣት ሕዉሃት ኢህአዴግ አብሮት ተወልዶ አብሮት የሚኖረዉን የክፋት ጋኔል በአንድነትና በሕብረብሄራዊ ስሜት አጠመቀዉ ይህምም ሕዉሃትን እንደ ክፉ በሽታ ሲንጠዉና ስያንዘፍዝፈው እአርፍትም ሲያሳጣዉ በማናለብኝነት የሚገዛቸዉ የመረጃ ማሰራጫ አዉታሮች ለዘመናት የሰራበት የመከፋፈል እሳትና ጭድ የማድረግ ሴራና ስሌት እንዴት ሲደፈር አለ። ሆኖም ይህ የዘረኝነት ገመድ ዳግም ላይገመድ አንዴ በኦሮማራ ጉብሎችና ቄሮዎች ተጎምዷል!! የሁለቱ ማህበረሰብ አንድነት ዳግም ላይገርሰስ ስንጥቃቱን ለማሻር በደማቸዉ የታሪክ አሻራዎቻቸዉን አኖሩ ይህም ባሳለፍነዉ የሁለት አመታት በላይ ያለማቋረጥ የተካሄደዉ ሕዝባዊ እንቢተኝነት ፍም እሳት ዋናዉ ማገዶ አቀባይ ሆኖት ዘልቋል። ይህ የአንድነትና የአብሮነት የመቻቻልና የህብረበሄራዊነት ስሜት ከሕዝቡም አልፎ በሕዉሃት የበኩር ልጆች አህዴድና ብአዴን ቤቶችም በደማቁ ያለማቋረጥ ያንኳኳ ጉዳይ ከመሆንም አልፎ ዘልቆ በመግባት ይህ የህዝብ ትግልና ቁርጠኝነት ከስልጣን ይለቅ የሀገርን ጥቅም የማስቀደም ጥያቄ በአመራሮቹ የደም ዝዉዉር ዉስጥ በመግባት በትልቅ ከትኙበት እንቅልፍ ያነቃቸዉ ጉዳይ ከመሆነም አልፎ እስትንፋሳቸዉና የፖለቲካ ቅኝታቸዉ ሁሉ አንድነትን መሰርት ያደረገ ፍትህን ያስቀደመ የሕግ የአንድ ብሔር ሳይሆን የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ሀገር ትመሰረት ዘንድ እራሳቸዉን እንደ አብረሃም ልጅ ያቆብ ለመስዋእትነት በማቅረብ ሕዉሃት ለዘመናት የገነባዉን የጎሳና የብሔር ድልድይ ለመሻገር ያላቸዉን ቁርጠኝነት በተግባር ማሳየት ጀምረዋል። ለዚህም መሳካት የተጠናና የጋራ መተሳሰብን በሁለቱ ብሔሮች ለማጠንከርም ከሕዝቡ ጋር በመሆን ተግባርን መሰረት ያደረጉ ስራዎችን መስራት ከጀመሩ ከራርመዋል በተለይም

- ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ቄሮዎች “ጣና ኬኛ” ብለዉ ከኦሮሚያ ወደ ባህርዳር በመዉረድ በአንባገነኑ ድብቅ ሴራ እንዲሁም በእንቦጭ ላይ ዘምተዋል ይህ የተሳካ ይሆን ዘንድ የሁለቱ ማህበረሰብ ርዕሰ መስተዳድሮች ያደረጉት የተቀናጀ ስራም ዉጤቱ ያማረ እንዲሆን ቁልፍ ሚናን መጫወቱ

- ከዛም ስናልፍ በኦህደዱ መሪ አቶ ለማ መገርሳ የሚመረአዉ የኦሮሚያ ሉዑካን ቡድን  ከብአዴን አቻቸዉ ከአቶ ገዱ አንዳርጋቸዉ ጋር በጋራ መስራት ስለሚቻልበት ጉዳይ ለመምከር ባህርዳር ድረስ መዝለቃቸዉ
- ከዚያም ስንሻገር በተለያዩ ሕዝባዊና የድርጅት መድረኮች ያለምንም ማወላወል የጎሳ ሳይሆን የህዝብ የበላይነት መከበር እንዳለበት “በጎድ ፋዘር” የመራት ዘመን እንዳከተመ  ከንግዲህ በግልባጭ ደብዳቤ ትእዛዝ ክልሎች መተዳደሪያ ደንባቸዉን እንደማይቀይሩ በአንፃሩ ከህዝብ ጋር አብሮ በመቆም የህዝብን ፍላጎት በማስቀደም ለስልጣን ሳይሆን ለሀገር ደህንነት ቅድሚያ ለመስጠት ያላቸዉን ቁርጠኝነት የገለፁባቸዉ አጋጣሚዎችን መመልከቱ ....

በነዚህ ሁለት የክልላት መስተዳድሮች ዉስጥ የተፈጠረዉን የለዉጥ መነሳሳት ስሜትና ቁርጠኘንት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በሕዉሃት ኢህአዴግ ጡጫ የተሰነተቀውን የአንድነት በትር ለማሻር **ጀንፎና ና ጅና** በመሆን ህመሙን ለመፈወስ ቁስሉን እንዲጠግ ለማድረግ እስካሁን ለአንድነትና ለሕዝቦች ነፃነት ለፍትህና ለኩልነት ሲባል በፈሰሱ የንፁሃን ደም ጋር አንድ ላይ በማበር አስከፊዉን ስርዓት መገዳደርም ብቻ ሳይሆን አንገዳግደዉ ደደቢት ገደል ለመክተት መሰረቱን መናድ ከጀመሩ ሰነባበተዋል። እኛም ገልቱዎቹን እነ ወርቅነህ ገበየሁና ካሳ ተክለ ብርሃንን ካረጀ የዘረኝነት አስተሳሰብ አላቆ ልቦና ይስጣችሁ ስንል  ለአቶ ለማ መገርሳና ለአቶ ገዱ አንዳርጋቸዉ እንዲሁም አብረዋቸዉ በዚህ ትግል መድረክ ባልተንሸዋረረ አቋም ለቆሙት ሁሉ  ገለቶማ ማለት ወደናል።

ከዚህ ስናልፍ በተለይም የሰሞኑን የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ ስብሰባ የብአዴንና የኦህዴድ ቁልፍ አመራሮች በአንድነት በፅናት መዝለቃቸዉ እሱን ተከትሎም ከመንግስት ነኝ ባዩ ህዉሃት ኢህአዴግ መንደር የተሰማዉ የህሊና እስረኞችን የመፍታት ጭምጭምታ የመነሻዉ ሃሳብ ፍንትዉ አድርጎ የሚያሳይ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ሆኖም ይህ የህዝብ ትግል በተለይም የኋላ ኋላ እነ ለማን እነ ገዱን እነ አብይን እንዲሁም ስማቸዉን ለመዘርዘር የሚችግረኝ እልፍ የሁዋላ ደጀኖችን ያሳተፈዉ ትግል መነሻና መዳረሻ ጭብጡ የሕግ ታራሚዎችን ማስፈታት ሳይሆን ሕዉሃት ኢህአዴግ በህሊና እስረኛነት ግዞት ስር ያስቀመጣቸዉ እነ አንዱዓለም አራጌ፣ እነ አንዳርጋቸዉ ፅጌ፣ እነ እስክንድር ነጋ፣ እነ በቀለ ገርባ፣ እነ መረራ ጉዲና የታሰሩለት እነ አበበ ካሴ፣ እነ መቶ አለቃ ጌታቸዉ  በግፍ ተደብድበዉ የተኮላሹበት እነ ሃሊማ፣ እነ ንግስት እምነትና ሴትነታቸው የተዋረደበት  እንዲሁም እልፍ ህልቆ መሳፍርት የነብስ ዋጋ የከፈሉት ለመሞታቸዉ፣ ለመታሰራቸዉ፣ በግፍ ለመደፈራቸዉና ለመኮላሸታቸዉ ምክንያት የሆነዉ የዜጎች በእኩል የመተዳደርና የሕግ የበላይነት እንዲሁም በመንም መንገድ የምይደራደሩበት የአንድነት መሰርታችን የሆነችዉን ኢትዮጵያን ከጥፋት አዉሎንፋስ በማትረፍ ለሁላችንም የሁላችንም እኩል የሆነች ከልዩነታችን አንድነችን የበለጠባት ሀገር እንድትኖረን የሚለዉ ፅኑ አላማ ነዉና ይህንን ከግብ ለማድረስ ህዝብም በሕዉሃት ኢህአዴግ የተለመደ የሞኝ ዘፈን ሁል ግዜ አበባዬ አይነት ማደናገሪያ ሳይዘናጋና በተገኘዉ ድል በመርካት መዘናጋት እንደሌለብንና ከትግል ሜዳ እንዳንርቅ ማሳሰብ እወዳለሁ።  በተለይም የስርዓቱን የፈረጠመ ጡንቻ ሳይፈሩ ፊት ለፊት የተጋፈጡትን የዘመናችን ዳዊቶች በማጎበዝ ማገዝ በስነልቦናም በሃሳብም ማጠንከር ከዛም ሲያልፍ የህዉሃት መራር የበቀል እርምጃ ሰለባ እንዳይሆኑ ነቅቶ በመጠበቅ ትግላችን ግቡን መቶ በአንባገነኖች መቃብር ላይ ለመቆም እስከምንበቃ ትግላችንን አጠናክረን መቀጠል በተገኙት ድሎች መርካት ሳይሆን እንደ አቀጣጣይ ቤንዚን በመጠቀም በታደሰ ሞራል የስኬታችን መሰረት የሆነዉን ሕብረ ብሄራዊነትን በማንገብ ወደፊት መጓዝ ይኖርብናል።

በዚህ አጋጣሚ የፅሁፌ ጭብጥ በዋናነት ያጠነተነዉ በኦሮሚያና በአማራ ስለሆነ ትኩረቴን በዛዉ አደኩ እንጂ በዚህ የሞት ሽረት ትግል ዉስጥ በአራቱም ማዕዘን ያሉ እልፍ አእላፍ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያኖች በሀገራችን እኩልነትና አንድነት፣ ፍትህና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ከፊታችን በልበሙሉነት የሕይወት ዋጋ መክፈላቸዉንና እየከፈሉ መሆኑን ይህም ከምንም በላይ የሚያኮራና የአንድ ኩሩ ዜጋ ተቀዳሚ ተግባር መሆኑን መሆኑን ሳልጠቅስ ማለፍ አልወደድኩም( ደ.ህ.ዴ.ኖች ሰምታችኋል)። በመጨረሻም  ለሕዉሃት ኢህአዴግ መንግስት እንዲህ እላለሁ የህሊና እስረኞችን ሳይሆን ፍትህን ፍቱልን!! ማዕከላዊን ዝጉልን በማዕከላዊ ግፍ የፈፀሙትን ለፍርድ አቅርቡልን!! ፍርድ አልባ ፍርድ ቤቶችንም ዝጉልን!!

ኢትዮጵያዊነት በሀገር ወዳድ ዜጋ ደም ዉስጥ የሚኖር ሱስ ነዉ!!

መብራቱ ከስቶከሆልም